# የሴቶች እኩልነት ትናንት እና ዛሬ

ከሀይለማሪያም ወንድሙ 12-21-16

(hamariamwondimu@gmail.com)

ሥርዓተ ፆታ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሠጣቸውን ሚና፣ ባህሪ፣ አመለካከት እና ግምት በማኅበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ሞራላዊ ጉዳዮች ሁሉ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚወስን የሚወስን ነው። የሥርዓተ ፆታ ትርጓሜና ከአገር አገር ከመለያየቱም ሌላ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚቀያየር ነው።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሴቶች ላይ የሚደረጉ ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ የተናጠል እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ ቆይተው ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ የሴቶችን መብት የማስከበር ንቅናቄ በተደራጀ መልክ ወደ መድረክ ብቅ አለ። ንቅናቄው ትኩረት እያገኘ በመሄድም በ1954ዓ.ም ተ.መ.ድ. ባወጣው ቻርተር የሴቶችና የወንዶች የመብት ዕኩልነት ያፀና የመጀመሪያን ዓለም አቀፍ ስምምነት አጸደቀ። በአሁኑ ወቅት የሴቶችን መብት ለማስከበር ሠፋ ያለ ጥረት ቢደረግም የተ.መ.ድ ዘገባዎች እንደሚያሳዩት በየትኛውም የዓለም ክፍል  ሴቶች ከወንዶች ዕኩል መብታቸው የተከበረበተ ቦታ የለም።

በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደረጉ ሁሉን ዐይነት ትንኮሳዎችና ጥቃቶችን ለመከላከል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 57ኛ ጉባኤውን በአውሮፓያን አቆጣጠር መጋቢት 2013 ዩ ኤስ አሜሪካ፣ ኒውዮርክ አካሂዶ ነበር፡፡

በወቅቱ ከኢትዮፌያ የተወከሉት የቀድሞዋ የሴቶች፣ ህጻናት እና ሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ በጉባኤው ላይ ንግግር አድረገው ነበር፡፡ ወ/ሮ ዘነቡ በወቅቱ እንደተናገሩት በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ከሚደርሰው ጥቃት መካከል የቤት ውስጥ ጥቃቶች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ አስገድዶ መድፈር፣ ዕድሜያቸው ሳይደረስ ሴት ልጆችን መዳር እና ጠለፋን በዋናናት ጠቅሰዋል፡፡

በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርስ ጥቃት አሰቃቂ የሰብአዊ መብቶችን ከመርገጥ ተለይቶ እንደማይታይ እና ይህም  ገቢ አመንጪ ሥራዎች በሆኑ ዘለቄታዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፉ እንደሚገድብ ገልፀዋል፡፡ እንደሚኒስትሯ ገለፃ፣ እንደዚህ ዐይነት ጥቃቶች ተፅዕኖዎቻቸውን የሚያሳርፉት በተጠቂ ሴቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ላይ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የማህበረሰቡን እኩልነት በመሸርሸር፣ ምርታማነትን በመቀነስ፣ አጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ እና በሲቪል ሰርቪስ ሥራቸው ዘገምተኝነት የሚታይባቸው ሴቶች እንዲኖሩ የሚያደረግ ነው፡፡

በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚደርስን ሁሉን ዐይነት ጥቃትም ካልተወገደ ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማምጣት አይቻልም። ጤናማ እና የበለፀገ ማኅበረሰብ ለመፍጠር በሴቶች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ ይገባል፡፡ ሴቶች በእማወራነት ሚናቸው ልጆቻቸውን በኃላፊነት ስሜት፣ እንዲበቁ እና እንዲነቁ አድርገው ያሳድጋሉ። የማኅበረሰቡ ግማሽ አካሎች ከመሆናቸው አንፃር ድጋፍ፣ እንክብካቤ ፣ማበረታቻና ትብብር ሲደረግላቸው ደግሞ የበለጠ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ይተጋሉ፡፡ ቀስ በቀስም በተለያዩ አደረጃጀቶች በመሳተፍና በትምህርት

ራሳቸውን በማሳደግ የተቋማት ኃላፊዎች ለመሆን ጭምር ይታጫሉ፡፡ ኃላፊነታቸውን በሰከነ መንፈስ ስለሚወጡም ውጤታማ ሆነው ታይተዋል።

የኢህአዴግ ጊዜያዊ መንግስት ገና ደርግ በወደቀ ማግስት የአንድ ወር ሥልጣን ይዞ ከቆየ ጀምሮ የተሟላ ትኩረት የተሰጣቸው ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶች፣ መጀመሪያ በቻርተሩ ቀጥሎ በሕገ-መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ተከብረዋል። በአገራችን የሰውን ልጅና የማህበረሰቦችን መብት በማወቅና በማክበር ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲ ሰፍኗል፡፡ ከግለሰብ እስከ ቡድን መብት ድረስ ያሉ መብቶች እውቅና ተሰጥቷቸው የሕግ ጥበቃ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

በሕገ መንግሥታችን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ የመንቀፍም ሆነ የመደገፍ፣ የመደራጀት፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ፣ በሕይወት የመኖር፣ ከአካላዊ ጉዳት የመጠበቅ ወዘተ . . . ግለሰባዊ መብቶች ተከብረዋል፡፡ በቡድን መልክ የሚገለፁ ማኅበረሰቦችም የተሟላ እኩልነት ተጎናፅፈዋል፡፡ ሴቶች፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሠራተኞች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና የመሳሰሉት ማህበረሰቦች የቡድን መብቶቻቸው የሚከበሩበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

በኢፌዴሪ መንግሥት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስወገድ የቤተሰብ ሕግ በ1992 ዓ.ም እንዲወጣ ተደርጓል። በፀደቀው ህግ ጋብቻ የመመሥረት፣ የማስተዳደርና የማፍረስ ሂደት የሴቶችን ወሳኝ ተሳትፎና ሙሉ ፈቃደኝነት ባረጋገጠ ሁኔታ መካሄድ እንዳለበት አውጇል። በ1997ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የወንጀለኛ ሕግ ከ561 እስከ 570 ባሉት አንቀፆች በሴቶች ላይ ሲፈፀሙ የቆዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወንጀለኛነት የሚያስጠይቁ የወንጀል ድርጊቶች ሆነው ሰፍረዋል።

በአገራችን ሴቶች በዘውዳዊው የአገዛዝ ዘመናት፣ በተለይ በፖለቲካው ዘርፍ የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ እና ሊጠቀስ የሚችል አልነበረም፡፡ በዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ዘመን የነበሩት እቴጌ ጣይቱ በመጠኑም ቢሆን ስማቸው ሊጠቀሰ የቻለው በራሳቸው ጥረት አንዳንድ ውሳኔዎችን ለመወሰን በሚወስዱት ቆራጥ እርምጃ ነበር፡፡ በውሳኔዎቻቸውም ያላቸው ተቀባይነት እየጎለበተ  መሄድና ስመጥር ሊያደርጋቸው በቅቷል፡፡

በወታደራዊ የደርግ የአገዛዝ ዘመን ሴቶች የነበራቸው ሚና ከዘውዳዊው አገዛዝ የተለየ አልነበረም። በወቅቱ “ማርች 8” ወይም “የሴቶች ቀን” ሲከበር ቢቆይም አገዛዙ ርዕዮተ ዓለሙን ከማስተጋባት ውጪ ለሴቶች ዕኩልነት ያመጣው ፋይዳ አልነበረም፡፡ ስርአቱ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር (አኢሴማ) የሚል የሴቶች ማኅበር ቢመሠርትም እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ አላመጣም። በወቅቱ ሊጠቀስ የሚችል የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎም  አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ከደርግ ይልቅ የደርግን አገዛዝ ለመጣል ሲጥሩ የነበሩ ታጋዮች ሴቶችን አሳትፈው የአርነት ትግል በማካሄዳቸው የደርግን አምባገነን አገዛዝ ገርሥሰው በመጣል  የዴሞክራሲያዊ አገዛዝን መሥርተዋል፡፡

ወታደራዊው አምባገነን አገዛዝ ከወደቀና ኢህአዴግ ስልጣኑን በኋላ በ1985 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት አማካይነት የሴቶች ፖሊሲ ፀድቋል። ለዚሁ ሲባልም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ

የሆነ የሴቶች ጉዳይ ት/ቤት ተቋቁሞ ነበር። በዓመቱም የሴቶችን መብት ለማስከበር መሠረታዊ መብቶችን ያካተተ ብሔራዊ የሴቶች ፖሊሲ እንዲወጣ ተደርጓል።

በ1987 ዓ.ም የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ሴቶች በሀገሪቱ ማኀበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ከወንዶች ዕኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማይተካ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህም ሕገ-መንግሥቱ ላይ የወጣውን ድንጋጌ ወይም አንቀጽ ሊያፀኑ የሚችሉ ተቋማዊና መዋቅራዊ አሠራሮች ለመዘርጋት ጥርጊያ መንገዱን ያመቻቸ ነው፡፡

ሴቶች ላይ ከሚደርሱ አድልዎ፣ ማግለልና የመሳሰሉት ጥቃቶች በተጨማሪ የተለያዩ የስነ-ልቦና ጫናዎችን ማሳደረም ቀደም ሲል ከሚታዩ ጥቃቶች ጋር አብረው የሚጠቀሱ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህልም ከምሳሌያዊ አባባሎቻችን መካከል "ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ"፣ "ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት" የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ሲሆን በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ደካማ አባባሎቻችን ናቸው፡፡

ቀደም ሲል በሴቶች ላይ ይደረሱ የነበሩ ተፅዕኖዎችን ከግምት ያስገባው ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 25 ላይ ፆታን መሠረት ያደረገ ማግለል በሕግ ፊት ተቀባይነት እንደማይኖረው ደንግጓል፡፡ "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት ዕኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸው ማንኛውም ዐይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል" በማለትም ያስረዳል። በመንግሥት የሥራ ተቋማት ሴቶችን ለማበረታታት በቅጥር፣ በዕድገት፣ በዝውውር፣ በትምህርትና ስልጠና እና በመሳሰሉት affirmative action (አዎንታዊ ድጋፍ)ሥርዓት ተዘርግቷል። ይህም በሥራ ቦታዎች የሴቶችን አቅም ለማጎልበት፣ ለማትጋትና ለማበረታታት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

በአንቀጽ 35 ላይም የሴቶችን ዕኩል ተጠቃሚነት ሲደነግግ የሥራ ቅጥርን እና የመሬት ባለቤትነትን ጨምሮ በሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሴቶች ከወንዶች ጋር ዕኩል መብት እንዳላቸው በሠፊው በመግለፁ ብቻ ሳይሆን የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ማኀበራዊ ጥቅሞችን ለማክበር የሚያስችሉ በዘልማድ ሲደርስባቸው የነበረውን አድልዎና ጥቃት ለመከላከል የሚረዱ ድንጋጌዎች አስፍሯል። በተጨማሪም ለረጅም ዘመናት ሰፍኖ በቆየው አሠራር ከወንዶች ዐኩል ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸውን በመሸረሸሩ የተወዳዳሪነት ብቃታቸው በሂደት እስኪጎለብት ድረስ የሚዘልቁ አዎንታዊ ርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ደንግጓል። ቀደም ሲል ሴቶች በትዳር ላይ እያሉ ከትዳር አጋራቸው የሚደረስባቸው ጫና እና በደል ሰልችቷቸው ትዳራቸውን የሚያፈርሱ ከሆነ ያላቸው አማራጭ ትዳራቸውን ጥለው፣ ልብሳቸውን አንጠልጥለው ወደ ቤተሰቦቻቸው መመለስ፣ በዘመድ ቤት መቀመጥ አሊያም በሰው ቤት መቀጠር ነበር፡፡

የኢፌዴሪ መንግሥት እነዚህንም ችግሮች ለመቅረፍ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን አውጥቷል ፡፡ ከነዚህም አንዱ የቤተሰብ ሕግ ነው፡፡ አንዲት ሴት ትዳሯን ለማፍረስ የምትገደድበት ሁኔታ ቢኖር ቀደም ሲሉ በነበሩ ድንጋጌዎች ሴቶች ቤታቸውን ጥለው እንዲወጡ ይደረግ ነበር፡፡ በተሻሻለው ሕግ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ አንድ ሴት ትዳሯን ብትፈታ እንኳን እሷ በቤት ቀርታ

ባለቤቷ ቤቱን ጥሎ እንዲወጣ የሚያስገድድ ሕግ ወጥቷል፡፡ ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀም እና ንብረታቸውን የማስተላለፍ መብታቸውም በመከበሩ በኢኮኖሚው በኩል ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት እየላቀ ወጥቷል።

በኢ.ፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ለሴቶች በተሰጠው ትኩረት በማኅበረሰቡ ብሎም በራሳቸው በሴቶቹ የነበረው አመለካከት እንዲቀረፍና ማኅበራዊ የበታችነት፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት እና ፖለቲካዊ ሥልጣን አልባነት የሚወገድበት ሁኔታ ተመቻችቷል። በዓለም ላይ ለ24ኛ ጊዜ የተከበረው የነጭ ሪቫን ቀን በሀገራችን ሲከበር ለ10ኛ ጊዜ ሆኗል። ይህም በሴቶች የሚደርሰውን ጥቃት ለመቃወም እና ወንዶች ለሴቶች ያላቸውን አጋርነት ለመግለፅና ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠር ይረዳ ዘንድ ታስቦ የተደረገ ነው።

በኢ.ፌዴሪ መንግሥት የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲያድግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት ምንም አልነበረም ከሚባልበት ከዘውዳዊው እና ከወታደራዊው አገዛዝ ይልቅ ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ መጥቷል። በ1987 ዓ.ም የሴት ተወካዮች ም/ቤት (ፓርላማ) አባላት ሁለት በመቶ ብቻ የነበረ ሲሆን ከአሥር ዓመት በኋላ ቁጥሩ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ከ38 በመቶ በላይ ደርሷል። በርካታ ሴት አስፈፃሚ አካላትም ወደ ውሳኔ ሰጪነት ደረጃ መጥተዋል። የሴቶች በራስ የመተማመን እና ሀሳብን በድፍረት የመግለፅ ክሂሎትን ለማዳበር የሚረዳ ሥልጠና በተለያዩ ተቋማት ሲሰጥ መቆየቱም ለሴቶች የተሰጣቸውን ትኩረት ያሳያል።

በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሴቶችንና የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃትና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሴቶችንና የወጣቶችን ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል አቅጣጫ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልፆ ነበር፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን በዕቅዱ ዘመን የሴቶችና ወጣቶችን ፓኬጅ አጠናክሮና አቀናጅቶ ተግባራዊ በማድረግ የሴቶችና ወጣቶች የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዕድሎች እንዲሰፉና እንዲጠናከሩ እንዲሁም የሴቶች አመራር ሰጪነት ተሳትፎ እንዲጠናከር ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል፡፡

በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 8ነጥብ6 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴቶች በግብርና እና ከግብርና ውጪ ባሉ የሥራ መስኮች ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር 11ነጥብ11ሚሊዮን ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፤ 3ነጥብ4 ሚሊዮን ሴቶች የሥራ ጫናን ለመቀነስ በሚያስችል በአማራጭ ኢነርጂ እና በሌሎች የተለያዩ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ ሥራ አጥነት እየቀነሰ፣ ገቢያቸው እያደገ መጥቷል። በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ በንግድ ሥራ አመራር 1ነጥብ 13 ሚሊዮን፣ በየደረጃው በተካሄዱ የግንዛቤ እና ንቅናቄ ሥራዎች 2ነጥብ2 ሚሊዮን ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ እና 1ነጥብ8 ሚሊዮን በራስ አገዝ ማኅበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ ሆነዋል። ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ከማድረግ እና የቁጠባ ባህላቸውን ከማዳበር አንፃር የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

ላይ እንደተገለጸው የሴቶችንና ወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ በሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ግንባታ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች በተደራጀ መልኩ የነቃ እና ግንባር ቀደም ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከውጤቱም በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡

የሴቶችና ወጣቶች ፓኬጆች ትስስርና ተመጋጋቢነት በአለው ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በአገሪቱ ያሉ የተለያዩ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የልማት ዘርፎች የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ከግምት ያስገቡ እንዲሆኑ የተመቻቸ ሲሆን ሴቶች በማኀበር ተደራጅተውም ሆነ በግል በብድርና ቁጠባ አገልግሎትም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በጥቃቅን እና በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ጨምሮ በክልሎች ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት እና ለማጎልበት በስልጠና፣ ብድር አቅርቦት፣ ገበያ ትስስር፣ በማመምረቻና መሸጫ ቦታዎች ግንባታ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የአዲስ አበባን እና የድሬዳዋን ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ በክልሎች ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት እና ለማጎልበት በብድር አቅርቦት፣ በስልጠና፣ በገበያ ትስስር፣ በማምረቻ እና በመሸጫ ቦታዎች ግንባታ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ በርካታ ሴቶችን ተጠቃሚ ያደረገ ሥራ ተሠርቷል። ከሁለት ዓመት በፊት በአዲስ አበባ በግማሽ በጀት ዓመቱ ብቻ 335 የማምረቻ እና መሸጫ ክፍሎች፣ ለ3ሺህ 294 ተጠቃሚዎች የተላለፉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 35 በመቶ የሚሆኑት ተጠቃሚዎች ሴቶች ነበሩ። በዚሁ ወቅት በንግድ ሥራ አመራር ሥልጠና 114ሺህ 421 ወንዶች እና 88ሺህ 282 ሴት አንቀሳቃሾችን ለማሰልጠን ተችሏል። በተመሳሳይ ቴክኒክ እና ክሂሎት ሥልጠና 38ሺህ 992 ወንዶች እና 22ሺህ 67 ሴቶች ሠልጥነዋል።

በአነስተኛ ብድር እና ቁጠባ ብዙ ሥራ አጦች እና ሥራቸውን ማስፋፋት የሚፈልጉ ዜጎች የብድር አገልግሎት ተመቻችቶ እየተሠራ ይገኛል። በዚህ በኩል የሴቶች ተጠቃሚነት እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። በዘርፉ የሴቶችን ተሳትፎ ከነበረበት 35 በመቶ ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተይዞ በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተፈጠረው የሥራ ዕድል የሴቶችን ድርሻ 39 በመቶ ማድረስ ተችሏል። በስልጠና በኩል የሴቶች ተሳትፎ 42 በመቶ የብድር ተጠቃሚነታቸውም 48 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል።

በጤና ረገድ ለእናቶችና ለህፃናት በተሰጠው ትኩረት ዜጎች በአቅራቢያቸው በሚገኙ ቀበሌዎች የሕክምና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የጤና ኬላዎች በቀያቸው እንዲከፈቱ ተደርጓል። በ2005 ዓ.ም ግንቦት ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ በሥርዓተ ፆታ፣ በእናቶች ጤና እና በሥነ-ተዋልዶ ላይ ትኩረት ያደረገ "Women Deliver" በሚል በማሌዥያ መዲና ካላላምፑር ታላቅ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር። በጉባኤው ላይ በሴቶች ሕይወት ላይ ለውጥ ያመጡ ስድስት አገሮች ይፋ ሲደረጉ ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ ተሸላሚ ነበረች። ማሌዥያ፣ ኬንያ፣ ኔፓል፣ ባንግላዴሽ እና ዑራጋይ ተከታዮች ናቸው።

ኢትዮጵያ በዚህ ጉባኤ ላይ የተመረጠችው ለሥነ-ተዋልዶ አገልግሎት መስፋፋት ከፍተኛ ጥረት ስላደረገችና ትልቅ እመርታን በማሳየቷ ነው። በተለይ መንግሥት ከ30ሺህ በላይ የጤና ኤክስቴንሽን በማሠልጠን እና በማሠማራቱ የጤና አገልግሎት አሠራሩን እንዳሻሻለው ተጠቅሷል። ከሃያ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥነ ተዋልዶ የወሊድ መከላከያን የሚጠቀሙት በትዳር ውስጥ ካሉ ሴቶች 3 በመቶ ብቻ ነበሩ። በወሊድ ጊዜ የሚሞቱ እናቶች ቁጥርም ከዓለም የመጀመሪያ ደረጃ ይዞ ቆይቶ ነበር።

ባለፉት አሥርት ዓመታት በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በመታገዝ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በእጥፍ ካሳደጉ ሦስት አገሮች አንዷ መሆኗን ሰነዶች ይጠቁማሉ። በዚህ አገልግሎትም ብዙዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። እናቶች ከልምድ አዋላጆች ከመጠቀም ይልቅ በህክምና ተቋማት እንዲወልዱ እና እንዲጠቀሙ ምቹ የአገልግሎት ስርአት ተዘርግቷል።

በአጠቃላይ፣ ያነሳናቸው ነጥቦች መንግሥት ለሴቶች የሰጠውን ትኩረት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያገኘውን ተቀባይነት የሚያሳዩ ናቸው። ከጠንካራ ወንዶች ጀርባ ጠንካራ ሴቶች አሉ እንደሚባለው ሴቶችን መደገፍ እና ማበረታታት የሚጠቅመው ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ወንዶችን፣ ብሎም አጠቃላይ ማኅበረሰቡን ነው።